ዴሞክራሲያ
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

**ዴሞክራሲያ ቅጽ 38 ቁጥር 3** **ታህሣስ 2005 ዓ.ም**

## *ሳይደራጁ ትግል*
## *ሳይታገሉ ድልን መቀዳጀት መቼ ታይቶ?*

ተደጋግሞ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዴሞክራሲ ሥርአት ባልተመሰረተባቸው ሕብረተሰቦች ቀርቶ በተመሰረተባቸው አካባቢዎች እንኳ ለሰብአዊ እድገት መዳበርና መጎልበት፡ የሲቪሉ ማህበረሰብ አስተዋፅዖ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው። ይህ ሲባልም ያለምክንያት አይደለም። በኤኮኖሚ ከዳበሩ ሀገሮች ሕዝቦች የእድገት ታሪክ የተገኘው ትምህርትና በኛም ሀገር ከተማሪዎች እንቅስቃሴ በተለይም ሥር ነቀል ከሆነው ሕዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ የተገኘው ተመክሮ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ይኸውም በማንኛውም ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥም ጭምር የፖለቲካ መረጋጋትን አረጋግጦ በእድገትና በብልፅግና ጎዳና ለመጓዝ ብሎም የዴሞክራሲ ሥርአትን እንዲሁም የሕዝብ ሙሉ ውክልና ያለው መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የሲቪሉና የሙያ ማህበራት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ለዴሞክራሲ መመስረትም ሆነ ግንባታ ወሳኝ ከሆኑት እሴቶች መካከል በነጻ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብት ያለገደብ መከበርና ተግባራዊ መሆን በዋናነት የሚጠቀሱ መሆናቸው ግልፅ ሲሆን ኢሕአፓን የመሰረቱትም ሆነ በሂደትም የተቀላቀሉት አባላቱና ደጋፊዎቹ ለዚህ መርህ አጥብቀው እየታገሉለት የሚገኙት ይህን ሁለንተናዊ እውነታ ከግንዛቤ በማስገባት ነው። ካለፉት ተመክሯችንም ሆነ ከቅርቡ ታሪካችን እንደምንገነዘበው ይህ መብት የማስከበር ጥያቄ ከፖለቲካ ድርጅቶች ባሻገር በተለይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚኖረው ለሲቪልና ሙያ ማህበራት ነው። የዚህ ምክንያቱ ልዩ ሚስጢር ሆኖ ሳይሆን ሕዝባዊ ድርጅቶች ባጠቃላይ ነፃነታቸው ከተከበረ በማንኛውም ጊዜና ወቅት በአስተዳደሩና በሕዝቡ መካከል በአገናኝነት የሚሰሩና ከሕዝቡ በቀጥታና በቅርበት የተለያዩ ተግባራትን ሊያከናውኑ የሚችሉ በመሆናቸውም ነው። በተለያዩ ሁኔታዎች የተደራጁ በተለይም ደግሞ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፤ የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና መዳበርና ለፍላጎቶቹ መሟላት የሚታገሉና የሚንቀሳቀሱ የሲቪልና የሙያ ማህበራት አምባገነን ሥርአትን ለመጣል በሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግልም ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። እንደ ኢሕአፓ ከመሰለ በሕዝብ ከተደገፈና ከታቀፈ ቆራጥ ከሆነ ታጋይ ድርጅት ጋር የሚኖራቸው ቅርበትና ግንኙነትም ወሳኝነቱ የሚገለፀው በዚሁ ክስተት ብቻ ሳይሆን ብዙሃኑን ሕዝብ በትግሉ ለማሳተፍ መሰረቱና መመዘኛውም ይኸው በመሆኑም ጭምር ነው። የሰራተኛም ሆነ የመምህራን፡ የሴቶችም ሆነ የወጣቶች፤ የተማሪዎችና የጋዜጠኞች፡ የጭቁን ወታደርና ሌሎችም እንቅስቃሴ ከዚህ አንፃር በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

እነዚህ ድርጅቶች ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ዘርፈ ብዙ በሆኑ ግንኙነቶች የተሳሰሩ ናቸው። የነሱ ጥንካሬ ለሕብረተሰቡ እድገት ከፍተኛ ምሶሶና ፀጋ መሆኑ በርካታ ተመክሮዎች የሚያስተምሩት እውነታ ነው። በሕዝብ ለተመረጠና የሕዝብን ውክልና ላገኘ ሕዝባዊ አስተዳደር ደግሞ በመንግስትና በሕዝቡ መካከል በድልድይነት ለማገልገል ከመቻላቸውም በላይ በቅርበት የሚሰሩ በመሆናቸውም የሕዝብን ፍላጎት፡ ጥቅምና ችግር፡ ብሶትና ደስታ ለመገንዘብ ከመንግስት በበለጠ አመቺ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ናቸው። ለዚህም ነው በተለያዩ ግብረ ሰናይ ተግባራት፡ በኤኮኖሚና በፖለቲካ ዘርፎች፡ በእድገት እንቅስቃሴዎች፤ በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃና በተፈጥሮ እንክብካቤ መስኮች የተሰማሩና

ወደፊትም መሰማራት የሚፈልጉ የሲቪልና የሙያ ድርጅቶች ሁሉ ተግባሮቻቸውን በነፃ የማከናወን መብታቸው እንዲጠበቅ አበክሮ የሚጠየቀውና ልዩ እንክብካቤና ድጋፍም የሚለገሳቸው።

ሁኔታውን ጠለቅ አድርጎ የሚመለከት ማንኛውም ለሕዝብ ቀናኢ የሆነ ዜጋ ሁሉ ሊገነዘብ እንደሚችለው በሲቪል ማህበራትና በመንግሥት መካከል የሚኖረው ግንኙነት መመስረት የሚገባው በዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ ነው። በርግጥም ከሁሉ አቀፍ ድህነት፡ ከኋላቀርነት፡ ከሰላም መደፍረስና ከማህበራዊ አለመረጋጋት፡ ከብሔራዊ ፀጥታ መጓደልና ከባዕድ እርዳታ ተመፅዋችነት ለመውጣት ያለው እድል ይኸው ብቻ ነው። በተለይም ከባዕድ እርዳታ ተመፅዋችነት ለመላቀቅ ወሳኙ ተዋናይ ሕዝብ ራሱ ነውና የፈጠራ ችሎታውን በመጠቀም የሀገሪቷን የሰው ኃይል፡ ልምድ፡ ጉልበትና እውቀት ሆነ የሚያስፈልገውን ብሔራዊ የገንዘብና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም በተገቢ ሁኔታ ለማንቀሳቀስ ባለው ቁርጠኝነትና ዝግጁነት የሚወሰን በመሆኑ ነፃነትን የተላበሱና ከአገዛዙ ቁጥጥር የተላቀቁ የተለያዩ የሲቪልና የሙያ ማህበራት ተሳትፎ ወሳኝ ለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

ከዚህ አንፃር ሕዝባችን መብቱን በቆራጥ ትግል አስከብሮ በተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች መካከል የሚገኙትን ልዩ ልዩ ጥቅሞቹን አቻችሎ ለመኖር የሚያግዘው ሕገ መንግሥታዊ ሥርአት በነፃነትና በፍላጎቱ ለመመስረት ምንም እንኳ ባለፉት በርካታ አመታት በትግሉ ከፍተኛ የንብረትና የአካልም ሆነ የሕይወት መስዋዕቶችን ቢከፍልም እስካሁን አልተሳካለትም። ወያኔ/ኢሕአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ እንደ ደርጉ የፖለቲካ ሥልጣኑን በብቸኝነት ጨምድዶ ይዟል። በዘር ክፍፍል ላይ ተመስርቶ የዘረጋው የፖለቲካ ሥርአትም ለሁሉም ሕጋዊና አስተዳደራዊ መንገዶችም ሆነ ዴሞክራሲን ለማስፈን ለሚጥሩ ኃይሎች ሁሉ እንቅፋት እንጂ እገዛ የሚያደርግ ሆኖ አልተገኘም። ወያኔ ገና ከውልደቱ የጨበጠው የአብዮታዊ ዴሞክራሲና የዘረኝነት ራዕዩ አሁንም ተጠናውቶት ስለሚገኝ ለዴሞክራሲ መመስረትና መዳበር የራሱን አስተዋፅዖ አበርካች ኃይል ሊሆን አልቻለም። ችሎታ ባይኖረውም በሂደት እየተማረ ለመሥራት እንኳ ፍቃደኛ ሆኖ አልተገኘምም። የተመሰረተበት አመለካከቱና ራዕዩ የተነሳም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የማይቻለውና ፍላጎትም የሌለው መሆኑንም ከበቂም በበቂ አመስክሯል።

በርግጥም ወያኔ የሕዝብን ፍላጎት በመፃረርና መብቱንም በመርገጥ የፖለቲካ ሥልጣኑን በባዕዳን ድጋፍ ከጨበጠ ጊዜ አንስቶ ከሀገር ወዳድ ኃይሎች በኩል በተደጋጋሚ የቀረበለትን የእርቅና የሰላም ጥሪ በንቀትና ዕብረት ውድቅ በማድረግ የአፈናና የሙብት ጥሰት ተግባሮችን ማከናወኑን ተያያዘው እንጂ በሀገራችን መብትን አስከብሮ፡ ሰላምን አሰፍኖ ሕዝባችን ዴሞክራሲያዊ ባሕልን እንዲያዳብር መድረኩን አመቻችቶ በተረጋጋ ሁኔታ የእድገትና የብልፅግና ጎዳና እንዲጓዝ አላደረገም።

የወያኔ አገዛዝ ገና ከውልደቱ ጀምሮ የሲቪልና የሙያ ማህበራት ባጠቃላይ በሕብረተሰብ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና በተለይም ለዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መከበር የሚያደርጉትን አስተዋፅዖ አስመልክቶ የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዙና የተመሰረተበትም ራዕይ ይህንን ጭብጥ እንዲያይ ስላላደረገው ገና ከጥንስሱ የሲቪልና የሙያ ማህበራት እንቅስቃሴ አደጋ ያንዣበበት ነበር። በኋላም ወያኔ በየጊዜው የወሰዳቸውን የተሳሳቱ ተግባራት የሲቪልና የሙያ ማህበራት የማያቋርጥ ተቃውሞ በማድረጋቸው በተቃዋሚ ፓርቲ መልዕክተኝነት፡ የጥገኛ ምሁር ቁልፍ መሸሸጊያና መፈልፈያ፡ የዴሞክራሲ ግንባታ እንቅፋት“ ተፈርጀው በወያኔ ይደርስባቸው የነበረው ጫና ከፍተኛ እንደነበረም አይዘነጋም። ግለሰቦችን ከማሰር ጀምሮ በተግባር የወሰደው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ከፍተኛ በመሆኑ የሲቪል ማህበራት በዚህ በኩል ሊያደርጉት የሚችሉት ተሳትፎ ከምንጊዜውም በላይ እየቀነሰ መምጣቱና የኋላ ኋላ ለወያኔ አላማ አስፈፃሚነት መዳረጋቸው የሚያስገርም አይሆንም። በተለይ የሽብርተኝነትና የሲቪልና የመረዳጃ ማህበራት ሕግ ከደነገገ ጊዜ ጀምሮ ነፃነታቸውን መነጠቅ ብቻ ሳይሆን የመንቀሳቀሻ ንዋይ ማጠር ጋር ተደምሮ ሕልውናቸው አጠያያቂ ደረጃ በመድረሱ አብዛኛዎቹ ከመድረኩ ለመገለልና ድርጅታቸውን ለማፍረስ ተገደዋል።

በዚህም የተነሳ በመልካም አስተዳደር እጦትና በሙብት አለመከበር ምክንያት የሚከሰቱ እንደ ሙስና፡ የፍትህ መጓደል የመሳሰሉት ነቀርሳዎች በሕዝብ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያደርሱትን መጠነ ሰፊ ጉዳቶች በመታደግና በመከላከል በኩል የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዳያበረክቱ ተደርገዋል።

ይህ ብቻ አይደለም። ዜጎች የተሟላ አኗኗር እንዲኖራቸው በሚያስችሉ መሰረታዊ የሕዝብ አገልግሎቶች መስከም ሆነ ባጠቃላይም ድህነትን ለመቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንዳያደርጉ ወያኔ እንቅፋት ደቅኖባቸዋል።

ወያኔ ነፃነታቸውን ጠብቀው ለመንቀሳቀስ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩትን የሲቪልና የሙያ ማህበራት ሲቻለው በኃይል እያፈረሰ ሳይቻለው ደግሞ መሪዎቻቸውንና ንቁ አባሎቻቸውን በማሰር፡ በማስፈራራት፡ በመግደል፡ ለስደት በመዳረግ አዳክሞ በሱ አምሳያ ተለጣፊ ከጎናቸው መጠፍጠፍ አይነተኛ መለያው ነበር አሁንም ነው። የአስተማሪዎች፡ የሰራተኞች፡ ኢሰመጉ፡ የነፃ ፕሬስ ተቋማትና ሌሎችም በርካታ የሲቪል ድርጅቶች የዚህ መሰሪ ፖለቲካው ሰለባ ነበሩ፡ ናቸውም። የነዚህን ድርጅቶች እንቅስቃሴ በማንኛውም መልኩና መስኩ ለሕዝቡ በሚጠቅም ደረጃ ማቀነባበር፡ ማበረታታና መደገፍ ሲገባ በወያኔ/ኢሕአዴግ በርካታ አመታት በከንቱ ማለፋቸው የሚታወስ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ወያኔ ራሱ በደነገገውና ባወጣው ሕግ እንኳ ለመመዝገብና ሕጋዊ ሰነድ ለማግኘት የፈልጉ የሲቪል ድርጅቶች ውሳኔ ሳያገኙ ረጅም አመታት ማስቆጠራቸው የሚዘነጋ አይደለም። በ2005 ዓ.ም. ምርጫ ወቅት የሲቪል ማህበራትን እንቅስቃሴና ሕልውና ለአደጋ ያጋለጡ ድንጋጌዎች፡ ሕጎችና ደንቦች የምናስታውሳቸው በቁጭትና በሀዘኔታ ነው። የነዚሁ ሁሉ ችግሮች ምንጭ ደግሞ የመልካም አስተዳደር እጦት እንደነበርና በዚሁ ከቀጠለም ወደፊትም የከፋ ችግር ሊከሰትባቸው እንደሚችል ቀደም ብሎ ኢሕአፓ በተለያዩ ጊዜያት ለሕዝብ ይፋ ባደረጋቸው መግለጫዎቹ አማካኝነት ለሕዝብ በይፋ ገልፆ ነበር። በርግጥም የተከሰተው ይኸው ነበር። ምርጫውን ተከትሎ በተከሰተው ሁኔታም በርካታ የፖለቲካና የሲቪል ድርጅቶች መሪዎችና አባሎች እንዲሁም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶች ከታሰሩ በኋላ ቀደም ብሎ በቋት ላይ የነበሩትም ሆነ የሚደርስባቸውን ችግር ተቋቁመው አብሮ ለመሥራት ፍቃደኛ የነበሩትም ጭምር አፈናው ከድጡ ወደ ማጡ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ካለው ከፋኛ የመጠራጠር ጠባዩና ሁሉንም ከመቆጣጠር ካለው ፍላጎቱ ሲቪል ድርጅቶች በራስ አነሳሽነት በሚያደርጉት ማናቸውም ግላዊ እንቅስቃሴና የኤኮኖሚ ተሳትፎ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳደረ ብቻ ሳይሆን ሕልውናቸውንም አጥፍቷል። የወያኔ አገዛዝ በልማት ቅድሚያም ሆነ በብሔራዊ ደህንነት በማሳበብ የሲቪልና የሙያ ማህበራት እንደ ሕይወት እስትንፋስ የሚያስፈልጋቸውን የዜጎችን ነፃነት ከፉኛ ደፍጥጧል። የሀሳብ ነፃነት፡ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ፡ የመሰበሰብ እንዲሁም ዜና የማግኘት መብታቸውን ሽብርተኝነትን መከላከል በሚል አሁንም ድረስ አፍኗል።

ይህንን ማንኛውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ይህንን በቸልታ ሊመለከተው አይገባም። ለነፃነት መከበር፡ ለዴሞክራሲ መመስረትና መገንባት፡ ለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚታገል ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ ለሲቪል ድርጅቶች የመደራጀትና ተደራጅቶም በነፃ የመንቀሳቀስ መብታቸው እንዲከበር ባላሰለሰ ጥረት መታገልና ለነሱም የትግል አንድነት ማሳየት ይጠበቅበታል። የሲቪል ድርጅቶችም በበኩላቸው በሚሰማሩበት መስክ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ እንዳለ ሆኖ ከፖለቲካ ነፃ ነን፡ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊ አይደለንም የሚለውን እንቶ ፈንቶ በማስወገድ የወያኔ/ኢሕአዴግን አምባገነናውና ኢዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ለማስወገድ ከሚታገሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ይህ እውን እንዲሆን የትግል አንድነት በመፍጠርና በመረዳዳት በአንድ ላይ ሊቆሙ ይገባቸዋል።

ለዚህ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት አፅንዖት በመስጠት በተደጋጋሚ እንደተገለፀውና አሁንም እየተገለፀ እንደሚገኘው የሲቪልና የሙያ ማህበራት እንዲደራጁ መቀስቀስ፡ ተደራጅተውም እንዲታገሉና በስፋት በትግሉ ሂደት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ለትግሉ ወሳኝነት ይኖረዋል። ኢሕአፓ ባለፉት ጊዜያት እንዳደረገው ሁሉ ወደፊትም በዚሁ ጎዳና ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋፅዖ ከማበርከት ወደኋላ የሚል አይደለም። የነሱ መጠናከር የትግሉም የድርጅቱ መጠናከር ነውና። በኛ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ መድረኩ ከተመቻቸለት ከአብራኩ በሚፈልቁና ከአገዛዙ ነፃ የሆኑ የሙያ ማህበራት በማቋቋም ራሱ በራሱ ወደ ተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ለመሸጋገር ብቃቱና ብስለቱ እንዳለው በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ለመሆኑ ቅንጣት ታህል እንጠራጠርም። ታዲያ ፍላጎቱ ሰምረው እንዲገኙለት አሁንም እንደ በፊቱ እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ የወያኔ አገዛዝን ከሥልጣን ለማስወገድ በተከታታይ የሚያደርጋቸውን ትግሎች ቀጣይነትና ፅናት በተሞላበት መልክ ከመቀጠል ሌላ ምንም አማራጭ የለውም።

በተለያዩ ጊዜያት ለመጠቆም እንደተሞከረውም ሰብአዊ እድገትን ለማስገኘት መሰረቱ ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ መልካም አስተዳደርን መመስረት ነው። በተግባር በወያኔ አገዛዝ እንደምናየው ተጠያቂነት ከሌለ የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበርም ሆነ ለማረጋገጥ ዋስትና ሊኖር አይችልም። ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባልተከበሩለት የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ለመኖር የተገደደ ሕዝብ ደግሞ የአገዛዙን ሕጎች ጥሶ ካልሆነ በስተቀር ሰላሙን አግኝቶ የመንፈስ እርጋታን ተጎናፅፎ ማድረግ የሚፈልጋቸው እንቅስቃሴዎቹን በነፃነት ማከናወን አይችልም። መብቶቹ በገደብ የታጠሩ ከሆነ ደግሞ ጨርሶውኑም የሚከስሙበት ሁኔታ ነው የሚኖረው። ይህ ሁኔታ ሲከሰት ዘላቂ የሆነ እድገት ማግኘቱ ከባድ ነው። ለዚህም ነው ለወያኔ ሕግ አልገዛም ብሎ ሕዝባዊ አመፅ ማካሄድ የሰላም መልዕክት ሆኖ የሚገኘው። ሰላም የሙብት መከበር ውጤት ነው ተብሎ ተደጋግሞና ተበክሮ የሚገለፀውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ራሳቸውን በምርጥነት የሚመድቡ ምሁራኖችና የለውጥ ኃዋሪያ ነን ባዮች የሲቪልና የሙያ ማኅበራት በፖለቲካው መስክ የመሳተፍና የመወሰን ሂደትን በመጥለፍ በግላዊ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ከቻሉ በሰብአዊ እድገቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደር ብቻ ሳይሆን በዴሞክራሲና በፍትህ መካከል ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት ከፉኛ ያዛባል። ይህ ደግሞ በደርግ ዘመንም ሆነ በወያኔ የታየ ሐቅ ነው። ሰለሆነም ዜጎቹን ማዕከሉ የሚያደርግ ሥርአት በራሱ በሕብረተሰቡ አባላት መገንባት ይኖርበታል እንጂ እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ በተለይም ደግሞ የራሳቸውን የኤኮኖሚ ጥቅም በማስቀደም ጣልቃ ገብ ከሆኑ ሀገሮች የሚሸመት ሊሆን ጨርሶ አይችልም። የሌሎች የእንግሊዝ፡ ጀርመን፡ ፈረንሳይ፡ ሆላንድ ወዘተ ሀገሮችን የተወሰኑ የሕገ መንግሥት አንቀፆችን እንደ ወያኔ በመቅዳት እድገት የሚገኝ ጨርሶ ሊሆን አይችልም።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱ የሚንከባከባቸው፡ እንደ አይን ብሌኑ የሚሳሳላቸው፡ ተግባራቸውን በሚገባ የሚያከናውኑ፡ በሕዝቡ ተመርጠው ለሕዝቡ የሚቆሙ፡ የፖለቲካ ድርጅቶችና ከመንግሥት ጣልቃ ገብነትና አመራር ነፃ የሆኑ በተለይም መንግሥትንም ሆነ ከፍተኛ የግል ኤኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በአንክሮ የሚመለከቱና ለፖለቲካ ተሳትፎ አማራጭ መስኮችን ለማቅረብ የሚያፈላልጉ የሲቪልና የሙያ ማህበራት መኖራቸው ለሀገሪቷም ለሕዝቧም በጣም ወሳኝ ነው።

ነፃ የሲቪሉና የሙያ ማህበራት መኖርና መጠናከር ዴሞክራሲ ባሕልንና የመቻቻል ጠባይን የሚያዳብር ነው። እነዚህ እሴቶች እንዲዳብሩና እንዲጠናከሩ ዜጎች በፖለቲካው ሂደት ውስጥ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸው የእውቀት አድማስ ማስፋት ማለት ነው። ከመንግሥት ጣልቃ ገብነትና ቁጥጥር ነፃ በመሆን የሚደራጁ የሲቪልና የሙያ ማህበራት የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴና ተሳትፎ የሚያጎለብቱና የሚያግዙት ስለሆነ ልዩ እንክብካቤ ማግኘት የሚገባቸው ናቸው። ሲቪላዊነትን የተላበሰ ማህበረሰብ ሲባል የሚሰጠው ግንዛቤ የዜጎች ተካፋይ መሆንን፡ ለዴሞክራሲ መስፋፋትና መጠናከርን፡ ለማህበራዊ አንድነትና ለበለጠ መተባበርን፡ እርስ በርስ መተማመንን፡ ብሎም መረዳዳትን፡ ለሲቪላዊ ግንኙነት እያንዳንዱ ዜጋ በተለያዩ ደረጃ ለሚቋቋሙ ማህበራዊ ድርጅቶችና በፍላጎቱ አባል እንዲሆን ማበረታታትን፡ በደልና የፍትህ መጓደል በተከሰተበት እንዲታረም ለማድረግ ሲቪል ወኔነትን ለመላበስ ጥረት ማድረግን፡ ልምዶችንና ተመክሮዎችን ማዳበርን ነው። ሲቪላዊ ማህበረሰብ ድክመት በታየበትና ለውጥ ባስፈለገበት ሁሉ የሕብረተሰቡንና የመንግሥት ተግባራት በአዲስ ጎዳና እንዲጓዝ፡ ለተወሳሰቡት የሕብረተሰቡ ችግሮች መፍትሄ ማፈላለግ ሲሆን ከላይ ወደታች በትዕዛዝ የሚወሰን ሳይሆን ዜጎች በሙያቸው፡ በጥቅማቸው፡ በሕዝብና በወገን ተቆርቋሪነታቸው፡ በሌሎች ምክንያታዊ አነሳሽነት በመደራጀት ለመንቀሳቀስ ጥረት የሚያደርጉበት መድረክ ነው።

ሲቪላዊ ማህበረሰብ በጣም ብዙ የሆኑ ተግባራት የሚከወኑበት፡ ዜጎች ፍላጎታቸውንና ጥቅማቸውን በመግለጽ ዝግጁነትና ችሎታ ላይ የሚመሰረት፡ ለአቅመ ደካማዎችና እንክብካቤ ፈላጊዎች ልብን መስጠትና ከራስ ለተለየ ሀሳብ ደግሞ መቻቻልን የሚያንፀባርቅ ነው። ለዚህ ሁሉ ደግሞ በቅድሚያ የራስን መብት ለማስከበርና ነፃነትን ለመጎናፀፍ ከፍተኛ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። በየትኛውም ሕብረተሰብ ግላዊ ነፃነትን መጎናፀፍ ማለት በዜግነት ይሁን በሕብረተሰብ ደረጃ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን ግላዊና ተፈጥሯዊ መብት ለማስከበር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የሚገልፅ ሲሆን ይህ ኃላፊነትና ግዴታ ደግሞ በምሁራኑ በአዛውንቱ፡ በደራሲያን፡ በኃይማኖት አባቶች፡ በሀገር ወዳዱ፡ በሲቪሉና የሙያ ማህበራት መሪዎችና ንቁ አባሎቻቸው ሲንፀባረቅ በአርአያነት እንድንመለከታቸው የሚያገለግል መሆኑን

የሚገልፅ ነው። በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ በመሪነት ደረጃ የተሰለፉትን ብቻ የሚመለከት አለመሆኑንም የሚያሳይ ነው።

አምባገነኖችና የጥላቻ ቀፍቃፊዎች የሕዝብን ጎራ ለመከፋፈል፡ አንድን ዜጋ ሆነ የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍልን በሌላው ላይ ለማነሳሳት ከሚጠቀሙባቸው መሰሪ ተንኮሎች አንደኛው የሲቪሉና የሙያ ማህበራት መድረክ በመሆኑ ከሀገር ወዳዱ በኩል ልዩ ትኩረት መስጠትንም የሚያሻ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች የሲቪክና የሙያ ማህበራትን በግል ቁጥጥራቸው ለማስገባት ወይም እንደ ወያኔ ልምድ ተለጣፊ ለማድረግ መሞከር እንደሌለባቸውም ከዚሁ ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ነው። ከዚህ አንፃር የማህበራቱ ነፃነት መከበር አለበት ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን ፍሬ ያለው ትግል ለማካሄድ ድርጅቶች ታጋይም አዋቂም እኛ ነን በሚል የሲቪክና ሙያ ማህበራትን ወይም ሕዝብን በቀጥታ ያላሳተፈ ትግል ለማካሄድ መጣር የሌለባቸው መሆኑንም የሚጠቁም ነው። ስለዚህም በትግሉ የሲቪክ ማህበራትና ተቋማት እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ማህበራቱ በራሳቸውም እየታገሉ ስለሆኑና የሕዝብም ስብስብ በመሆናቸው በሀገር አቀፉ ትግል ተሳትፏቸውና ሚናቸው መረጋገጡ ወሳኝ ነው። ሕዝብን ማሳተፍ ስንል የድርጅት አባልና ሚናን ለመጥቀስ ብቻ ሳይሆን በዋና መልኩ ሰፊውን ሕዝብ በሲቪልና ሙያ ማህበራት አማካኝነት የትግሉ አካል ማድረግን የሚመለከት ነው። ይህ የሕዝብ ተሳትፎ በተለያዩ ጊዜያት በቅርቡም በግንቦቱ ምርጫ ታይተዋል። የድርጅቶች የትግል መሪነት ሚና የሚከሰተው ሰፊውን ሕዝብ ማለትም ብዙሃኑን በትግሉ ሊያሳትፉ ሲችሉም ነውና በዚህ በኩል ግንዛቤ መዳበር እንዳለበትም የሚያመለክትም ነው።

ለትግሉ ስኬታማነት ደግሞ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በትግሉ እንዲሳተፉ ማድረግ ወሳኝ ነውና የሲቪል ማህበረሰብ የሚሰጠው ግንዛቤ ሰርቶ አደሩንና አርሶ አደሩን ማዕከል በማድረግ ምሁራንን፡ የሙያ ማህበራትን፡ ጋዜጠኞችን፡ ደራሲያን፡ ተማሪና መምህራን፡ ሴቶችን፡ የኃይማኖት ዕምነት ተከታዮችን አደራጅቶና አንቅቶ ለትግል ማሳተፍ መሆኑን የሚገልፅ ነው። የሕዝብ ትግል ተጠናክሮ እንዲወጣና ሕዝብ ከሙያና ከሲቪክ ማህበራት ጋር የቅርብ ትስስር እንዲኖረው ለማድረግ ለማያያዝና ለማቀላለፍ ሕዝብን የማደራጀትና በትግሉም ንቁ ተሳትፎና ትብብር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የተቃዋሚ ድርጅቶች አቢይ ሚና መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በሕዝባዊ ሰላማዊ አመፅ ወያኔን ማስወገድ የሚለውን መተከላዊ መርህ የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው።

ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ከእድገት ጋር በጥብቅ የተያያዙ ናቸው። ለኛ ዴሞክራሲ በየጊዜው እያዳበረና እያደገ የሚሄድ ሂደት ሲሆን ይህም ሕዝብ የርስ በርስ ግንኙነቱን በራሱ ፍላጎት በተደራጀ መልክ መምራትን፡ የወደፊት እጣውን መወሰንን፡ በፖለቲካ ውሳኔ ተካፋይ መሆኑን ማረጋገጥን፤ የግለሰብንም ሆነ የማህበሩን እምቅ ኃይል ለተሻለና ዘላቂነት ላለው እድገት በዴሞክራሲና በእኩልነት መርህ የጋራ ውሳኔና እቅድ ላይ መሰማራትን የሚጠይቅ ነውና ከዚህ አንፃር ለሕብረተሰቡ ኃላፊነት በተለያዩ ባለድርሻዎች ትከሻ እንዲከፋፈል ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በቅድሚያ እንቅፋት የሆነ ኃይልን ማስወገድና ሂደቱ እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል።

በፊትም ሆነ አሁን በኛ እምነት የሲቪክ ማህበራት የጠላትና የአምባገነን ፖለቲካ ሰለባ እንዳይሆኑ በማስተማር በማደራጀት፡ በመቀስቀስ፡ በተመቸበት በግልፅ፡ ባልተመቸበት ሁኔታ ደግሞ በህቡዕ ደረጃ በደረጃ ትግላቸውን ማስፋት፡ ማጎልበት ማስተባበር ከዴሞክራሲና ከእኩልነት ጋር የማይነጣጠለው የሀገር ወዳድነት ኃላፊነታችንና ግዴታችን ነው። ለሀገር ሉዓላዊነት ቅድሚያ ሰጪነት ባሕሪያችን ደግሞ ሌላው የማንነታችን መገለጫ ነውና በዚሁ ትግላችንን በፅናት እንቀጥልበታለን። ይህም በመከፋፈል ሳይሆን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚያፈቅሩና በተጨባጭ በቦታው መልክ ባለው ሁናቴ ከሚንቀሳቀሱት ጋር በመተባበር፡ በመፈረካከስ ሳይሆን በመዋሃድ፡ በመነጣጠል ሳይሆን በአንድነት ነውና በዚሁ መንፈስ እንዲሁ በፅናት እንቀጥልበታለን። በዚህም ከሲቪክ ማህበራት ጋር የነበረን አብሮ የመጓዝ ቃል ኪዳናችን የማንነታችን ገላጭ ነውና ዛሬም ሕያው መሆኑን በትግላችን እናስመሰክራለን።

ሕይወት ካላቸው የሲቪል ድርጅቶች ውጭ ዴሞክራሲን ለመገንባትም ሆነ ለማጠናከር የማይታሰብ ነውና ድርጅቶቹ ከወያኔ/ኢሕአዴግ መዳፍ ሥር ተላቀው በነፃ እንዲደራጁና በትግሉም በስፋት

እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የሁሉም ሀገር ወዳድ ተግባርና ኃላፊነት ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን። በመሆኑም በሕብረተሰቡ ውስጥ ለተረሱ፡ የተበደሉና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለተነፈጋቸው ክፍሎች ድምፅ ሆነው እንዲጮሁ መቀስቀስ፡ ማደራጀት አግባብነት ያለው የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው። አይና ያወጣ የመሬት ነጠቃንና ገበሬን ከቀዬው ማፈናቀልና ለከፋ ብዝበዛ መዳረግን አንስቶ ምርጥ ለሆኑ ጥሬ ምርቶች፡ የአየርና የተፈጥሮ እንክብካቤ፡ ለሰብአዊ መብት መከበር፡ ለዴሞክራሲ መመስረት፤ የሰርቶአደርና ላባደር ብዝበዛን ለመገደብ፡ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ለማርገብ፡ ለዖታ እኩልነት መረጋገጥ፡ መጥፎና ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ፡ የጋራ እሴቶች የሆኑት ሰላምና ፍትህ እንዲሰፍኑ፡ ለሕዝብ ያላቸውን ቅርበትነትና ዝምድና ይበልጥ ለማጠናከርና ለማጎልበት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ለማበርከት የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲመቻችላቸው መታገል ወቅቱ የሚጠይቀው ሀገራዊ ግዴታ ነውና ይህ ስምሪት እንዲያገኝ አጥብቀን እንታገላለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

እናቸንፋለን!!